# ዘመን ቆጠራ ለቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን ዘመን ቆጠራ ያስፈለጋት በዓላትና አጽዋማት በየዓመቱ የሚውሉበትን ቀን ለማወቅ ነው። ሁለት ዓይነት በዓላት አሉን። ዓይነታቸውን ሁለት ያደረገብን የትንሣኤ ጉዳይ ነው። አንድን በዓል ዓመቱን ጠብቆ በዓመቱ በዚያው ዕለት ማክበር የተለመደ ነው። ለምሳሌ ቅዱስ ሚካኤል የሚከበረው ኅዳር 12 ቀን ነው። ባመቱ ባመቱ ኅዳር 12 ሲመጣ የሚካኤል ቀን ብለን እናከብረዋለን። ኅዳር 12 ቀን ከሳምንቱ ዕለቶች በየትኛውም (ሰኞ፣ ማክሰኞ... ወዘተ) ሊውል ይችላል። በሆነው ዕለት ቢውል ግድ የለንም፤ ያንን ዕለት የሚካኤል በዓል አድርገን እናከብረዋለን። ትንሣኤን ግን በዚያው ክርስቶስ ከሞት በተነሣበት በእሑድ ቀን እንዲሆን ፈለግን። እንዲህ ከሆነ በየዓመቱ በዓሉ የሚውልበት ወር በገባ በተወሰነ ቀን ለምሳሌ፤ በዚያው ከሞት በተነሣበት ዕለት በመጋቢት 29 ቀን ልናደርገው አንችልም። ጥንቱ ትንሣኤ እሁድ መጋቢት 29 ቢሆንም መጋቢት 29 ቀን ሁል ጊዜ እሑድ ቀን አይውልልንም፤ ከሳምንቱ ቀናት በማንኛውም ዕለት ሊውል ይችላል። ስለዚህ ክርስቶስ ከሞት የተነሣበትን ዕለት እሑድ መሆኑን ከረጋገጡ በኋላ በየዓመቱ በእሑድ ዕለት ሊያደርጉት ወሰኑ። ይኽ እንዴት ሊሆን ይችላል? ሁለትፈሉን (መጋቢት 29ንም እሑድንም) አይሆንም። ቀኑስ እሑድ መሆኑን በምን ዐወቁት?

ክርስቶስ ከሞት የተነሣው እሑድ ዕለት መሆኑስ አያጠራጥርም። አንደኛ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ክርስቲያኖች በአፍ ታሪክ ያቆዩልን ቀን ነው። ሁለተኛው ምሁራን ሐዲስ ኪዳንን ሲመረምሩ ክርስቶስ የተሰቀለው ዓርብ ዕለት፣ ከሞት የተነሣው ዓርብን ጨምሮ ከሦስት ቀን በኋላ በመጣው እሑድ ዕለት መሆኑን ተረድተዋል። እንዴት? እንዴት ማለት መልካም ነው። ፋሲካ የአይሁድ በዓል እንደሆነ እናውቃለን። እኛ ክርስቲያኖች ትንሣኤን "ፋሲካ" የምንለው የአይሁድ ፋሲካ ለክርስቶስ ሕማማትና ትንሣኤ ትንቢት ስለነበረው ነው። ጌታን ደቀ መዛሙርቱም (ተማሪዎቹ) አይሁዶች ስለነበሩ እንደማንኛውም ይሁዲ በዓሉን እንዳከበሩ አንብበናል (ለምሳሌ; ማቴ ም. 26)። ይኽ የሆነው ጌታን ለፍርድ ለማቅረብ በያዙበት ሳምንት ውስጥ ነው። ዕለቱ ኀሙስ ነበረ ለማለት ይቻላል። ያን ዕለቱን ማታ ወታደሮች መጥተው ጌታን ሲጸልይ አግኝተው ያዙት (በዚህም ዕለቱ ጸሎተ ኀሙስ ይባላል)። በማግሥቱ ክህነ ግርው ከጲላጦስ እንጠናዊው ላይ ክስ መስርተው ስቅላት አስፈረዱበት፣ ወዲያው ሰቀሉት። በቅዳሚ ቀን ምንም ሥራ ስለማይሠሩ ሬሳውን ያን ዕለታውኑ (በሰንበት ዋዜማ) ከሰዓት በኋላ ከመስቀል አውርደው ቀበሩት (ማር. ም.15 ቁጥር 42 እስከ 47)። እንደ ሀገሩ ልማድ ሴቶች በመዳቹ በሳልስቱ እሑድ ዕለት (በሰንበትም መጨረሻ በመጀመሪያው ቀን) ወደመቃብሩ ቢሄዱ መቃብሩን ባዶውን አገኙት (ማቴ. ም.28)። "በሰንበት መጨረሻ" ማለት ተርጓሚ ሳያስተካክለው ቀርቶ ነው እንጂ "በሳምንቱ መጨረሻ" ማለት ነው። ሳምንቱ የሚጨረሰው ከቅዳሚ በኋላ ነው። ከዚያ ቀጥሎ "በመጀመሪያው ቀን" ይላል። "መጀመሪያ ቀን" ማለት "እሁድ" ማለት መሆኑን ቀደም ብለን ተናግረናል። ማዕዙማ በቀጥታ "ወበእሑድ ሰንበት" ነው የሚለው።

በ317 ዓ.ም. ኒቂያ ላይ የተሰበሰቡት 318 አበው ቅዱሳን ጳጳሳት ከሳለፏቸው ውሳኔዎች አንዱ ትንሣኤ ሁል ጊዜ እሑድ እንዲውል ነው። ይኽንን ለመድረግ ዓመቱን ጠብቆ ለዚያ (ለመጋቢት 29) በቀረበው እሑድ ማዋል በጣም በቀለለ ነበረ። እነሱ ግን ትንቢቱን ሁልጊዜ ሕያው ለማድረግ ሲሉ ከአይሁድ ፍሰሕ ጋር ያለው ግንኙነት ቋሚ እንዲሆን በማሰብ የአይሁድ ፋሲካ ከዋለበት ቀን በኋላ የሚመጣውን እሑድ የትንሣኤ መታሰቢያ እንዲሆን ወሰኑ። ትንሣኤ ዓመቱን ጠብቆ በዚያው ቀን መሆን ከቀረ ትንሣኤን ተከትለው የሚመጡ በዓላትና አጽዋማ ሁሉ (ለምሳሌ፦ ስቅለት፤ ጰራቅሊጦስ ወዘተ.) ከትንሣኤ ጋር ሲንፏቀቁ ሲኖሩ ነው።

ይኽ ውሳኔ ለክርስቲያኖች በሳለማዊ ችግር ፈጥሮባቸዋል፤ ምክንያቱም አይሁድ ፋሲሕን ጨምሮ በዓሎቻቸውን የሚያከብሩት ዘመንን በጨረቃ እየቆጠሩ ነው። በዚህ ምክንያት የአይሁድ ፋሲሕ በበሐይ እንደሚቆጠረው በዓመት ውስጥ በተወሰነ ቀን አይውልም። አሁን እንግዲህ የአይሁድ ፋሲሕ የሚውልበትን ቀን በየዓመቱ እየፈለግን ትንሣኤን ከፋሲሕ ጋር አዛምደን ማክበር ግድ ሆነ።

የአይሁድ ፋሲሕ እሑድ ቀን ቢውልስ? ይኽ ጥሩ አጋጣሚ ይሆናል የምንል እንገኝ ይሆናል። የኒቅያ ጉባኤ አበው ግን እንደዚህ አላዩትም። አይሁድ ክርስቶስን ስላልተቀበሉ እንዲያውም እሱን አሰቅለው እሱን የተቀበሉትን ክርስቲያኖችንም ስላሰቃዩ በተለይም ቅዱስ እስጢፋኖስን (የመጀመሪያውን ሊቀ ዲያቆን) በድንጋይ ወግረው ስለገደሉት እነሱ ፋሲሐቸውን ሲያከብሩ ክርስቲያኖች ትንሣኤን ከነሱ ጋር በዚያን ጊዜ አብረው እንዳያከብሩ ከለከሉ አብሮ መደሰት ይመስልብናል አሉ።

## በዘመን አቆጣጠር ከምዕራብ ክርስቲያኖች ለምን ተለየን?

ክብ የሆነ ነገር ሲሳል ከየትኛውም ቦታ ሊጀመር ይቻላል ብለናል። ዓውደ ዓመትም ይኸው ነው። ዋናው ነገር አንድ ታላቅ ታሪካዊ ድርጊት ፈልጎ እሱን መነሻ ማድረግ ነው። ለምሳሌ ሮማዊያን የሮም ከተማ የተቆረቆረችበትን ዘመን መነሻ አድርገውት ነበር። ታላቁ እስክንድር የነገሠበትም የዘመን መቁጠሪያ ሆኖ ነበር። የኛ ካህናትም "ዘመነ እስክንድር" በሚል ስም ይጠቀሙበት እንደነበር የብራና መጻሕፍታችን ይመሰክራሉ። ሶርያውያን የሮማውያንን የዘመን አቆጣጠር (ማለት በፀሐይ ቀጥር ለዓመቱ 365/6 ዕለት መስጠትን) ከሮማዊያን በተዋሱ ጊዜ የዓመቱን መጀመሪያ ("ርእስ ዓውደ ዓመት" ይባላል) ጥምቀት(ኦክቶበር) 1 ቀን ላይ አድርገውት ነበር። በኋላ የሰማዕታት መታሰቢያ እንዲሆን በ460 ዓ. ኦ ወደ መስከረም(ሴፕቴምበር) 1 ቀን ለወጡት። ግብፆችና እኛ ርእሰ ዓውደ ዓመታችንን በመስከረም ቀን ያደረግነው ይኸንን በመከተል ሳይሆን አይቀርም። የመጀመሪያ ጳጳሳችን ፍሬምናጦስ የሶርያ ሰው ነበር። ከሱ በኋላም ብዙ የሶርያ መነኮሳት ኢትዮጵያ መጥተው መንፈሳዊ አባቶቻችን ሆነዋል። የዓመቱን መጀመሪያ በመስከረም ማድረግን ከሶርያውያንም ሆነ ከግብፆች ብናገኘውም ጀማሪው በ46 ቅ.ክ.ሮምን ይገዛ የነበረው ቄሳር ዩልዮስ ስለነበር የዩልዮስ *ባሕረ ሐሳብ (Julian calander)* ይባላል።

እንደ እውነቱ ከሆነ ዓመትን (የአንድ ዓመት ዘመን) ምን ጊዜም ቢጀመር በወርና በቀን መከፋፈል አይቻልም በዘፈቀደ ካልሄድን በቀር ከ365 ዕለት ውጪ ያሉትን 5 ሰዓት ከ 48 ደቂቃ ከ46 ዳግሚት(ሰከንድ) ምን እናድርጋቸው? ቄሳር ዩልዮስ በ46 ቅ.ክ. (ቅድመ ክርስቶስ) በወጣው የዘመን አቆጣጠር ሥርዓት መሠረት ዓመቱን 365 ዕለት ከ6 ሰዓት አድርጎ ለአራቱ ወሮች 30 30 ዕለት ለአንዱ 28/29 ዕለት ለቀሩት ሰባት ወሮች 31 31 ዕለት መድበዋቸው 12 ቦታ ከፈለው 12 ወሮች መሆናቸው ነው። እኛ በዓመቱ ቀኖች ተስማምተን ቀኖቹን በወር ስንከፍል ተለይተናል። ዋናው ነገር ዓመቱ ቀኖች ተስማምተን ቀኖቹን በወር ስንከፍል ተለይተናል። ዋናው ነገር ዓመቱ ውስጥ ባሉት ዕለቶች መስማማታችን ነው፤

የቄሳር ዩልዮስ አከፋፈል አድልዎ ያለበት ይመስላል አንዳንድ ወሮች 31 ቀን ሲሰጣቸው አንዳንዶቹ 30 ብቻ ተሰጥቷቸዋል ያለምክንያት አይደለም። ዋናው ጥያቄ ግን ይህ ነው። ዓመቱን 365 ዕለት ከ5 ሰዓት ከ48 ደቂቃ ከ46 ዳግሚት(ሰከንድ) በመድረግ ፈንታ 11 ደቂቃ ከ14 ዳግሚት(ሰከንድ) ከየት አምጥቶ ነው 365 ዕለት ከ6 ሰዓት (365 ከ ¼) ያደረገው? ይኸን አከፋፈል (ይኸንን የሌሰ ጊዜን ጨምሮ መቁጠር) በ1582 ዓ.እ. የነበሩ (የኢየሱሳውያን) ሊቃውንት ሲመረምሩት ሁለት የጨመራቸው ትርፍ ደቂቃዎችና ዳግሚቶች ኢምንት ቢሆኑም በዘመን ብዛት ተጠራቅመው የሌለን 10 ቀን አምጥተዋል፤ ሁለተኛው የአደይን እኩል በዚያው ልክ (በ10 ቀን) አናግተው በመጋቢት 25 ቀን (march 2) በማረፍ ፈንታ ቀደም ብሎ መጋቢት 15 ቀን (march 11) እንዲያርፍ አድርገውት ነበር። በ1582 ዓ.እ. የሮም ፖፕ የነበረው ግሪጎሪ (13ኛው ጎርጎርዮስ) በስሕተት የተከማቹትን 10 ቀኖች ቆርጠ ጣላቸው። በዚያን ዘመን (በ1575 ዓ.ም.) ጥምቀት 1 ቀን የዋለው በ28 september(1582 ዓ.እ) ነበር በዚያ አካሄድ ጥምቀት 8 በoctober 5 ቀን እንዲሆን ሲጠበቅ ጳጳሱ ያንን ዕለት october 15 ቀን(ጥቅምት 8) ነው ሲል አሉ የለም ዛሬ october 15 ቀን(ጥቅምት 18) ነው ብሎ ዐወጀ። ከoctober 6 ቀን(ጥቅምት 9) እንሥቶ እስከ october 14 ቀን (ጥቅምት 17) ያሉትን ቀኖች መቸ ኖርንባቸውና ነው ዛሬ october 15 ቀን (ጥቅምት 18) ነው የምትለው? ቢሉት በየዓመቱ ላይ የሌለን ደቂቃና ዳግሚት እየጨመርን ኖረንባቸዋል አላቸው ይባላል። እኛ ኢትዮጵያውያን በምዕራባውያን አቆጣጠር ወሮቹ እኩል በአንድ ቀን የማይጀምሩት (በአሁኑ ጊዜ 10 ቀን ዘመኑ መርጣ ቢሆን በ 11 ቀን የሚለያዩት) በዚህ ምክንያት ነው።

አሁንም ቢሆን እኮ የዓመቱ ጊዜ ከ48 ደቂቃዎች እና ከ46 ዳግሚቶች(ሰከንዶች) በፍራክሽንም (በክፋፋይም) ቢሆን ችግሩ ይበልጣል። በየ4 ዓመት 366 ዕለት እንዲኖረው የተደረገው 24 ሰዓት የማይሞላውን ዘመን ሞልቷል በማለት ነው። አራተኛውን ዓመት አንድ ዕለት ያስጨመረለት ዘመን (ጊዜ) 23 ሰዓት ከ 15 ደቂቃ ከ4 ዳግሚት ብቻ ነው። ይኸ(24 ሰዓት ስላይደለ) አንድ ዕለት አይደለም። ያንን አንድ ዕለት (24 ሰዓት) ለማድረግ በዘፈቀደ 44 ደቂቃ ከ 56 ዳግሚት ተጨምሯል። እነዚህ ተጠራቅመው በየ400 ዓመት 3 ዕለት ይወጣቸዋል። ስለዚህ ምዕራባውያን በየ400 ዓመቱ አንድ ዕለት ሠግር (leap year) አያደረጉ ሦስቱን ግን መጣል ይኖርባቸዋል ስለዚህም ዓመቱን 365 ከ97/400 በማድረግ ተዘጋጅተዋል። በኛና በነሱ መካከል ያለው ልዩነት በዚያው ልክ እየሰፋ ሄዶ በ1582 ዓ.እ በመስከረም ወር የነበረው የ8 ቀን ልዩነት ዛሬ በዚያው በመስከረም ወር 11

ደርሷል። አርማትን ካልተቀበልን ልዩነቱ እየሰፋ ይሄዳል። የከዋክብትን ሂደት የሚያጠኑ ሊቃውንት (የአስትሮኖሚ ሳይንቲስቶች) የሒሳቡን ትክክለኛነት (ማለት የዩልዮስ ባሕረ ሐሳብ መስወጥ እንዳለበት) ተቀብለውታል።

ለዚህ ጎደሎ ለምሳሌ መጠቀስ የሚገባው ባሕረ ሐሳብ አለ። በ1079 ዓ.እ. ዑመር ኸያም የተባለው የታወቀው የፋርስ(ኢራን) ባለቅኔና የከዋክብት ሊቅ፤ የጸደይ እኩሌ ዓውድ የሚፈጀው ጊዜ ከ8/33 ቀን እንደሆነ አሳይቶ ነበር። ይህም ክፍለ ጊዜ( period) ከጎርጎርዮስም (365 ከ97/400) ሆነ ከዩልዮስ(365 ከ ¼) ክፍለ ጊዜ ይልቅ የጸደይ እኩሌን ትክክለኛ በታ ይጠብቃል። ፖፕ ጎርጎርዮስም ከመረጠው ክፍለ ጊዜ ይልቅ የዑመር ኸያም የ33 ዓመት መሻሉን ያውቅ ነበር።

በዚህ የ33 ዓመት ዓውድ መጠቀም ዘዴው ቀላል ነው። መጀመሪያ ዓመተ ምሕረቱን በ33 እንገድፈዋለን። ተረፈ(ትርፍ) ከ 0(ዜሮ) እስከ 32 ይሆናል። ተረፉ 0 ከሆነ ዓመቱ አይሠግርም። ተረፉ ከ 0 ከበለጠ ግን ተረፉን እንደገና በ4 እንገድፈዋለን። አዲሱ ተረፍ 0 ከሆነ ዓመቱ ይሠግራል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን አቆጣጠር በከፊል ከዩልዮስ ቄሳር ዘመን አቆጣጠር የተዛመደ እንደሆነ አመለከቸሰው። በከፊል ደግሞ በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ዘመን አቆጣጠር በተለይም ከዘመነ ሰማዕታት ጋር የተያያዘ መሆኑንም አይተናል። ዓመቱንም ሁላችንም እንደምናውቀው 30 ዕለት ያሉባቸው 12 ወሮችና የቀሩትን 5/6 ዕለቶች 13ተኛ ወር ጳጕሜ(ጳጉሜን) አድርገን ከፍለነዋል። አማርኛ ተናጋሪዎች 'ጳጉሜን' በማለት ፈንታ "ቋጕሜ" የሚሉት የ 'ጳ' ድምፅ በአማርኛ ስለ አልነበረ ነው። ('ጰ' በአማርኛ አለመኖሩን ያወቅነው 'ጰ' ያለበት አማርኛ ቃል ስለሌለ ነው። 'ጴጥሮስ' 'ጳውሎስ' 'ጰራቅሊጦስ' 'ጰንጠቆስጤ' 'ጳጳስ' 'ጠረጴዛ' በመሰረቱ አማርኛ አይደሉም።)

እኛ ኢትዮጵያዊያን ሆንን ምዕራባዊያን ዘመናችንን የምንቆጥረው ዓመተ ምሕረት(ዓ.ም.)ን ዓመተ እግዚእ (ዓ.እ.) የምንለው ከክርስቶስ ልደት ጀምረን ከሆነ ለምንድን ነው ክርስቶስ የተወለደበትን ቀን የወራችንና የዓመታችን መጀመሪያ ያላደረግነው? ምዕራባውያን ክርስቶስ በዲሴምበር 25 ተወለደ ይሉና ዓመታቸውን ከአንድ ሳምንት የበለጠ ጊዜ ካለፈ በኋላ በጃንዋሪ ይጀምራሉ። እኛ በታሕሳስ 29 ቀን ተወለደ እያልን። እኛ የክርስቶስን እድሜ ደብቀን ወጣት ልናደርገው 7/8 ዓመት ቀንሰንለት (ከረበናትን ከጸሐፍት) ጋር ስለነበረ እንደነሱ ሽማግሌ ለማድረግ ምዕራባውያን 7/8 ዓመት ጨምረውለት ነው?

መጀመሪያ የመጀመሪያውን ጥያቄ ለመመለስ ልሞክር፤ ክርስቶስ ታኅሣሥ በገባ በ29 ወይም በዲሴምበር 25 ተወለደ ማለት ክርስቶስ ከመወለዱ በፊት ዘመን ቆጠራ እንደ ነበረ ያሳያል በዚያን ጊዜ የኛ ወር ታኅሣሥ የነሱ ወር ዲሴምበር ነበረ። ክርስቲያኖች የክርስቶስን መወለድ ለዘመን ቆጠራ መነሻ ሲያደርጉት እስከዚያ የነበረውን ዘመን(የዓመቱ ቁጥር ብዛት) ጣሉት እንጂ የልደቱን ቀን ርእሰ ዓውደ ዓመት (የዘመን መለወጫ) አላደረጉትም። የዘመን መለወጫውን ጊዜና የወሮችን ስምና አካሄድ ሳይለውጡ በዚያው ቀጥለዋል። ስለዚህ በኛ አገማመት ክርስቶስ የተወለደው ታኅሣሥ 29 ቀን ዓ.ም. (ወይም ታኅሣሥ 29 ቀን 5501 ዓ. ዓ.) ነው። ከመስከረም 1 ቀን እስከ ታኅሣሥ 29 ቀን ዓ.ም. ያለው ዘመን (ከመስከረም 1 ቀን 5501 እስከ ታኅሣሥ 29 ቀን 5501 ዓ.ዓ. ያለው ዘመን) "ዓመተ ምሕረት" የተባለው ክርስቶስ የተወለደበት ዓመት ስለሆነ ብቻ ነው። አባባሉን ልንቀይረው አይገባም። አንድን ድርጊት በእንደዚህ ያለ ዓመተ ምህረት ተፈጸመ ስንል (ለምሳሌ የአድዋ ጦርነት 1888 ዓ.ም. ተፈጸመ ስንል) ድርጊቱን በዚያ ዘመን ውስጥ ተፈጸመ ማለታችን እንጂ በዚያ ዓመተ ምሕረት መጀመሪያ ላይ ተፈጸመ ማለታችን አይደለም።

እኛ ክርስቶስ በታሕሳስ 29 ቀን 1 ዓ.ም ተወለደ ስንል እነሱ በዲሴምበር 25 ቀን ቅድመ ክርስቶስ (ቅ.ክ.) ተወለደ አሉ። ልዩነቱ እየሰፋ መጥቶ ባሁኑ ዘመን በ13 ዕለት የተለያየነው ከላይ እንደገለጥሁት ፖፕ ግሪጎሪ ያስተካከለውን (ያረመውን) የቄሳር ዮልዮስ ዘመን አቆጣጠር ስላልተቀበልነው ነው።

አሁን ደግሞ ወደሁለተኛው ጥያቄ ልሂድ ክርስቶስ የተወለደበትን ዓመት አስመልክቶ እኛና ምዕራባውያን በ7/8 ዓመት የተለያየነው ክርስቶስን ወጣት ወይም ሽማግሌ ለማድረግ ሳይሆን ካለማወቅ በመጣ ስሕተት ምክንያት ነው። አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ቅድስት ማርያምን "ወለተ ነዳያን" (የድሆች ልጅ) እንደሚሏት ክርስቶስ የተወለደው ካንድ ደሃ ቤተ ሰብ ከመሆኑ ሌላ ዘመኑ ሰዎች በቤታቸው ሲወለዱ ዕለቱ በየቤቱ በመዝገብ በማይያዝበት ዘመን ነው። በኛም አገር ቢሆን በቤተ መንግሥት በመኳንንትና በምሁራን ቤት ካልሆነ በቀር ልጅ የተወለደበትን ዕለት መዝገብ መያዝ የተለመደው

የምዕራባውያን ትምህርት በቀመሰው ትውልድ ቤት ነው። በሕዝብ ዘንድ ግን "አድዋ በተዘመተ በዓመቱ ዐረፈ/ች" ፣ የሰባ ዘመቻ በሆነ በሶስት ዓመቱ ተወለደ/ች" መዘተ ነው የሚባለው። አገር ቤትማ ገበሬው "ልጅህ እድሜው ስንት ነው?" ሲሉት መልሱ ልጁ በረጀው ደበሎ ተቆጥሮ "3 ደበሎ ጨርሷል" ይሆናል። እንዱን ደበሎ አስረጅቶ ለመጣል ምን ያህል ጊዜ ይፈጅበታል? የክርስቶስ ቤተሰብ (ቅዱስ ዮሴፍና ቅድስት ማርያም) ክርስቶስ የተወለደበትን ቀን መዝግበውትም እንደሆነ መዝገቡ አልተገኘም።

በትንቢቱ መሠረት አይሁድ የክርስቶስን መምጣት ይጠባበቁ እንደነበረ ስለሚታወቅ እውነተኛው ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ብዙ ሰዎች "እኔ የምትጠብቁት ክርስቶስ ነኝ" በማለት አጭበርብረዋል። እውነተኛ ክርስቶስ ሲመጣ እሱም እንደሌሎች አንድ የሚያጭበረብር ሰው መስሏቸው ነበረ የሰቀሉትም በዚህ ምክንያት መሆኑን ተናግረዋል (ለምሳሌ ማቴ. ም. 27፣ ቁ. 39-44)። ኢየሱስ እውነተኛው ክርስቶስ መሆኑን ለመቀበል የዓለም ሥልጣናት ከሦስት መቶ ዓመት የበለጠ ጊዜ ፈጅቶባቸዋል። በዚያን ጊዜ ወደቁኑ ሄደው "ለመሆኑ ክርስቶስ የተወለደው መቼ ነው?" ብለው ታሪክ መመርመር ጀመሩ። ግን ብዙ ማስረጃ አላገኙም፤ ስለሱ የሚናገር መዝገብ አልተገኘም። እርግጥ ሄሮድስ የሚባል ንጉሥ ይሁዳን ይገዛ በነበረበት ጊዜ በሰማይ ላይ ትልቅ ኮከብ በታየበት ጊዜ (ሰብአ ሰገልን የመራቸው) የሮማው ቄሳር አውግስጦስ "እኔ የምገዛው ሕዝብ ሁሉ ይቆጠር " ብሎ ትእዛዝ በሰጠበት ዓመት መወለዱን በኢየሩሳሌም ላይ የተሾመው ሮማዊ ገዢ የጳንጤው (ጰንጤናዊ) ጲላጦስ በነበረበት ጊዜ መሞቱን (መሰቀሉን) ወንጌሎች ይመሰክራሉ። ግን ታሪክን መርምረው ዘመኑን ለነገሩን አበው ሊቃውንት በጃቸው የነበረው መረጃና ምናልባትም የነሱው ችሎታ በቂ ስላልነበረ የተወለደበትን ዘመን ሲቀምሩ ተሳስተዋል። አሁን በኋላ የተነሡ ሊቃውንት ምንጮችን በመመርመር ከዘመኑ ላይ ምዕራባውያን 7 ዓመት እኛ 15 ዓመት እንደተቀነሰንለት ይናገራሉ። እንደሁ ከሆነ የተወለደው በኛ 15 ዓመት በነሱ 7 ዓመት ጨምረን ዛሬ 1992 ዓ.ም./ዓ.እ. ነው። የሁለተኛው ሺህ ዓመት እግዚእ መጀመሪያ ነው ብለን ዘንድሮ የከበርነው ዕለት ባለፈ በሰባት ዓመቱ ነው።

ባሕረ ሐሳብ
የዘመን ቁጠራ ቅርሳችን ከታሪክ ማስታወሻ ጋር
ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ
1993 ከታተመው ላይ የተወሰደ።